## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት አደረጃጀትና አሰራር ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፵፩/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. **"ምክር ቤት"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት ነው፡፡

፫. **"ኮሚቴ"** ማለት አንድን ጉዳይ ለማከናወን እንደአስ ፈላጊነቱ በምክር ቤቱ የሚቋቋም አስተባባሪ፣ ቋሚ፣ ንዑስ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ ነው፡፡

፬. **"የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ"** ማለት በከተማው ከንቲባ የሚሰየም ሆኖ በመንግስት፣ በምክር ቤቱና በብሔ ራዊ ምክር ቤቱ የታላቁ የህዳሴ ግድብን በተመለከተ የሚቀመጡ አቅጣጫዎች እና ውሳኔዎች የሚያስፈ ፅምና የሚከታተል አካል ነው፡፡

፭. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፮. **"ብሔራዊ ምክር ቤት"** ማለት በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፬/፪ሺ፫ መሰረት የተቋቋመው የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ነው፡፡

፯. **"ጽሕፈት ቤት"** ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋመ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Addis Ababa City Government Council for the Coordination of Public Mobilization for Construction of the Ethiopian Grand Renaissance Dam Establishment Regulation No. 41/2011".

### 2. Definitions

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"City"** means the Addis Ababa City.
2. **"Council"** means the Addis Ababa City Adminstrations Coucil for the Coordination of Public Mobilization for the Construction of the Ethiopian Grand Renaissance Dam.
3. **"Committee"** means a coordinator, adhoc, standing or sub committee formulated by the council necessary for accomplishment of any activity.
4. **"Executive Committee"** means an organ appointed by the Mayor of the City to implement and follow up directions and decisions given to it by the Government, Council and National Council about the Grand Renaissance Dam.
5. **"Government"** means the Addis Ababa City Government.
6. **"National Council"** means the National Council for the Coordination of Public Mobilization for the Construction of the Ethiopian Grand Renaissance Dam established by Council of Ministers Regulation No. 244/2011.
7. **"Office"** means Office of the Council established by this Regulation.

፰. **“ሕዝባዊ ተሳትፎ”** ማለት በዓባይ ወንዝ ላይ ለሚሰራው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ድጋፍ እና የገንዘብ መዋጮ ለመሰብሰብ፣ ግንባታውን በስፋት ለማሳወቅ ወይም ለማበረታታት ታስበውብማናቸውም የሕብረተሰብ አደረጃጀቶች፣ በሙያ ማህበሮች ወይም ቡድኖች የሚዘጋጁ ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ ሰልፎች፣ የህዝብ ትርኢቶች፣የንግድና የመሳሰሉትን እንቅስቃሴዎች ያካትታል፡፡

## ፫. ? ???

፩. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ምክር ቤት በዚህ ደንብ መሰረት ተቋቁሟል፡፡

፪. ምክር ቤቱ የራሱ ጽሕፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

፫. ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለአዲስ አባባ ከተማ ከንቲባ ይሆናል፡፡

## ፬. ???

፩. በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ዙሪያ በከተማዋ ነዋሪዎች የተፈጠረውን መነሳሳት ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር በህዳሴው ጉዞ ግቦችና እሴቶች ላይ ብሔራዊ መግባባትን ለማጠናከር፤

፪. የህዝቡ ንቅናቄ በተደራጀ አኳኋን እየተመራ የታሪካዊው የህዳሴ ግድብ ግንባታ እውን እንዲሆን ህዝቦች የዜግነት ድርሻቸውን እንዲወጡ ለማድረግ በሂደቱ የከተማዋ ነዋሪዎች የቁጠባ ባህል እና በራስ የመተማመን መንፈስ በቀጣይነት የሚያዳብሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር፤

፫. በታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የተፈጠረውን የህዝቡን በጎ ስሜትና አቅም በላቀ ደረጃ ተጠቅሞ በከተማችን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥን ይበልጥለማረጋገጥ ተጨማሪ አቅም እንዲሆንማስቻል፤

፬. የከተማችን ነዋሪዎች በተለያዩ ሕዝባዊ ተሳትፎዎች የሚሳተፉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለግድቡ ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል፤

8. **“Public Mobilization”** means any organized activity by community based organizations, professional associations and any interested groups, including public meetings, rallies, exhibitions and bazaars aimed at soliciting support, raising funds for, promoting or advancing the national effort of the constraction of the Ethiopian Grand Renaissance Dam on the Abay river.

## 3. Establishment

1. The Addis Ababa City Government Council for the Coordination of Public Mobilization for the Construction of the Ethiopian Grand Renaissance Dam is hereby established.
2. The council shall have its own office.
3. The council shall be accountable to the Mayor of the City of Addis Ababa.

## 4. Objective

1. Strengthen the national consensus on goals and values of the ongoing renaissance by scaling up the societies initiation towards constructing the Ethiopian Grand Renaissance Dam;
2. Strengthen the spirit of self-reliance and saving culture among the people through fostering public participation in the process of the construction of the historical renaissance dam and making it real;
3. Ensure and enable additional capacity in the city political economic renaissance change up to the maximum level by using gained positive attitude and capacity of the public in the construction of the grand renaissance dam;
4. Facilitate conditions for the society to participate in public forums in order to enable them to contribute their own share in the construction of the dam;

፭. በከተማችን ነዋሪዎች የአባይ ወንዝ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት አስተሳሰብ እንዲዳብርና ልማታችንን ለማደናቀፍ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎችን በንቃት ለመመከት፡፡

፭. ?? ? ?? ?? ???

ይህ ደንብ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታን ለመደገፍ በከተማው በሚከናወን ማንኛውም ሕዝባዊ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

??? ???
?? ? ?? ?? ???? ? ????

፮. ?? ? ?? ?? ????

ምክር ቤቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል:-

፩. የምክር ቤቱ ጉባኤ፤
፪. ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤
፫. እንደ አስፈላጊነቱ የሚቋቋሙ ኮሚቴዎች፤እና
፬. የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት፡፡

፯. ?? ? ?? ?? ????

የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር ፩፻፶ ሆኖ የሚከተሉትን አባላት ያካተተ ይሆናል:-

፩. የከተማው ምክትል ከንቲባ--------------------ሰብሳቢ፤
፪. የከንቲባው የህዝብ ግንኙነት አማካሪ-----------------------------------------------------------ምክትል ሰብሳቢ፤
፫. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ (ያለድምፅ)----------------ፀሐፊ፤
፬. የከተማው ዋና ሥራ አስኪያጅ--------------------አባል፤
፭. የከተማው ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ-----------------አባል፤
፮. የከተማ አስተዳደር ቢሮዎች፣ ኤጀንሲዎች፣ ኮሚሽኖች፣የባለስልጣን መስሪያ ቤቶች፣የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት የከተማው የልማት ድርጅቶችና ሌሎች በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎች---------------------------------------------አባል፤
፯. የዓሥሩ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚዎች--አባል፤
፰. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካይ--------------------------------------------------------------አባል፤
፱. የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካይ-----አባል፤

5. Strengthen the thought of the society's equitable benefit of the Abay River and attentively distort anti-developmental forces.

5. **Scope of Application**

This Regulation shall be applicable to all participations and public mobilization in the City to support the construction of the Grand Ethiopian Renaissance Dam.

## PART TWO
## ORGANS AND MEMBERS OF THE COUNCIL

6. **Organs of the Council**

The council shall have the following organs:

1. The Council Assembly;
2. Executive Committee;
3. As may be necessary other established committee's and;
4. Office of the Council.

7. **Members of the Council**

Number of the council shall be 150 and include the following members:-

1. Deputy mayor of the City ---------------chairman;
2. The mayors public relation councilor--------------------------------------------------------deputy chairman;
3. Head of the office (with no vote) ------Secretary;
4. General manager of the City ---------------member;
5. Speaker of the City Council -----------------member;
6. City Administrations Bureaus, Agencies, Commisions, Authorities, Muncipal Service Organs, Developmental Organizations of the City and other similarly positioned heads ------------------ member;
7. Chief executives of all 10 Sub-cities ----- member;
8. Representative of governmental higher education; organs ----------------------------------------member;
9. Representative of private higher education organs ---------------------------------------------- member;

፲. ከየኃይማኖት ተቋማቱ ተወካይ ---------------------አባል፣

፲፩. የአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ተወካይ-------------------------------------------------------------------አባል፣

፲፪. የጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾች ተወካይ-------አባል፣

፲፫. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካይ----------አባል፣

፲፬. የቲያትር ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ-----------አባል፣

፲፭. የፊልም ባለሙያዎች ማህበር ተወካይ-------------አባል፣

፲፮. የሙዚቀኞች ማህበር ተወካይ------------------------አባል፣

፲፯. የወጣቶች ፌዴሬሽን ተወካይ -------------------አባል፣

፲፰. የሴቶች ፌዴሬሽን ተወካይ--------------------------አባል፣

፲፱. የነዋሪዎች ፎረም ተወካይ ---------------------------አባል፣

፳. የወጣቶች ፎረም ተወካይ-----------------------------አባል፣

፳፩. የሴቶች ፎረም ተወካይ------------------------------አባል፣

፳፪. የወጣቶች ማህበራት ተወካይ----------------------አባል፣

፳፫. የሴቶች ማህበራት ተወካይ--------------------------አባል፣

፳፬. የመምህራን ማህበር ተወካይ------------------------አባል፣

፳፭. የሙያ ማህበራት (የህግ፣ የጤና፣ የምህንድስና፣ የኢኮኖሚክስ እና የሌሎች ማህበራት)ተወካይ----አባል፣

፳፮. የሰራተኛ ማህበራት ተወካይ -----------------------አባል፣

፳፯. የአሰሪዎች ማህበር ተወካይ-------------------------አባል፣

፳፰. የአካል ጉዳተኞች ማህበር ተወካይ-----------------አባል፣

፳፱. የዕድሮች ህብረት ተወካይ --------------------------አባል፣

፴. የታዋቂ ሰዎች ተወካይ--------------------------------አባል፣

፴፩. የምሁራን ተወካይ -----------------------------------አባል፣

፴፪. የኢትዮጵያ አርበኞቸ ማህበር ተወካይ------------አባል፣

፴፫. የሥራ አሥፈጻሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ከተመለከተው በተጨማሪ የምክር ቤቱ አባል እንዲሆኑ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

10. Representative of religious organs ------member;
11. Representative of Addis Ababa Chamber of Commerce and Sectoral Associations -----member;
12. Representative of Micro and Small Scale Operators -------------------------------------------------member;
13. Representative of Non-governmental Organizations -------------------------------------------------member;
14. Representative of Theatre Professionals Association -------------------------------------------------member;
15. Representative of Film Proffetionals Association ------------------------------------------------member;
16. Representative of musician professional association ------------------------------------------------member;
17. Representative of Youth Federation ------member;
18. Representative of Women Federation-----member;
19. Representative of Public Forum -----------member;
20. Representative of Youth Forum-----------member;
21. Representative of Women Forum----------member;
22. Representative of Youth Associations- --member;
23. Representative of Wemen Associations---member;
24. Representative of Teachers Association---member;
25. Represntative of Proffesionals (law,health, enginering, economics and other professional associations)---------------------------------members;
26. Representative of Labour Associations –members;
27. Representative of Associatotion of Employer --------------------------------------------------------member;
28. Representative of Persons with Disabilities Association ------------------------------------member;
29. Representative of Edir Union --------------member;
30. Representative of Public Figure -----------member;
31. Representative of Intellectuals -------------member;
32. Representative of Ethiopian patriots Pssociation -------------------------------------------------------member;
33. The executive committee may allow additonlal members to be members of the council other than provided under this Article.

፰. ?? ? ?? ?? ???? ??

የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት:-

፩. ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ይኖረዋል፣
፪. በከተማው ከንቲባ የሚሾም አንድ የጽሕፈት ቤት ኃላፊና ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ኮንትራክት ሰራተኞች ይኖሩታል፣
፫. የምክር ቤቱን የዕለት ተዕለት የስራ እንቅስቃሴ ይፈጽማል፣ ይከታተላል፣
፬. የምክርቤቱን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣
፭. በሰብሳቢውየሚሰጡትንሌሎችተግባራት ያከናውናል፡፡

??? ???

??????????? ????? ? ?-? ???

፱. ?? ?? ?? ????? ????

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማስፈፀም በሰብሳቢው የሚቀርቡለትን የአጭርና የረዥም ጊዜ እቅዶች፣ መርሃ ግብሮች እና ፕሮጀክቶችን ያጸድቃል፣
፪. ከሚመለከታቸው ሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመመካከር እና በመቀናጀት መላው የከተማ ነዋሪ ለግድቡ ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርግበትን ስልት ይቀይሳል፣
፫. የህዝቡ ስሜት ግለቱን ጠብቆ እንዲሄድ የሚያስችሉ የንቅናቄ ሥራዎችን ውጤታማ በሆነ አግባብ እንዲፈፀም ማስቻል፣ በተለይም የህዝቡን ንቅናቄ ለማጠናከር የሚያስችሉ መድረኮች በከተማ፣ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳ፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና በግል ተቋማት ጭምር መድረኮች እንዲፈጠሩ ያመቻቻል፣
፬. ከግድቡ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ ልምድ እንዲሁም የሕዝቡን መልካም ስሜት በመጠቀም የከተማዋ ነዋሪ በተጀመሩት የልማትና የመልካም አስተዳደር ስራዎች እንዲሁም በሁሉም የሃገር ግንባታ መስኮች ተሳትፎውን እንዲያጎለብትና እንዲያጠናክር ያበረታ ታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

**8. Office of the Council**

The office of the council:

1. Shall have its own juridical personality;
2. Shall have head of office appointed by the mayor and the necessary contract staffs;
3. Shall have the duty to operate the day today activities of the council, and supervise the same;
4. Implement the decisions of the council; transfer the same for the appropriate organs;
5. Perform such other activities as may be assigned to it by the chairman.

**PART THREE**

**POWERS, DUTIES AND MEETIN PROCEDURES**

**9. Powers and Duties of the Council**

The council shall have the following powers and duties:

1. Approve long and short term plans, programs and projects designed for the implementation of objectives provided under this Regulation;
2. Design method in collaboration and coordination with the relevant public organs for the over all participation of the public for the construction of the dam;
3. Enable the proper implementation of effective movemental activities with the same sense of motivation, specially to strengthen the public movement by facilitating opportunities at city, sub-city, wereda, governmental and non-governmental organizations and private organs;
4. Encourage the public to strength the participation in all ongoing developmental and good governance activities by using their positive attitude towards the constriction of the dam;

፭. የከተማችን ነዋሪ በየአደረጃጀቱና በየተቋሙ የቁ ጠባ ባህል እንዲያዳብር ድጋፍና ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

፮. በከተማችን ከቦንድ ሽያጭ በተጨማሪ የሕዝባዊ ተሳ ትፎ እንቅስቃሴ በመጠቀም ተጨማሪ ገቢ እንዲሰበ ሰብ ያደርጋል፤

፯. በከተማዋ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ስለተሰበሰ በው የገቢ መጠን ከፌደራል መንግስትና ከብሔራዊ ምክር ቤቱ ጋር በመመካከር ለከተማዋ ነዋሪዎች እንዲገለጽ ያደርጋል፤

፰. የከተማችን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ የገቢ አሰባሰብ ሥርአት ከብሔራዊ ምክር ቤቱ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤

፱. የከተማዋ ነዋሪዎች ብሔራዊ መግባባትን እንዲፈጥሩና በፀረ ልማት ኃይሎች የግድቡን ግንባታ ለማደናቀፍ የሚ ከናወኑ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች የሚያመክን የህዝብ ግንኙነት ሥራዎች እንዲከናወኑ ይደርጋል፤

፲. ዓላማውን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ቋሚ፣ ጊዚያዊ፣ ወይም ንኡሳን ኮሚቴዎችን ያደራጃል፣ሪፖርታቸውን ያዳምጣል፤

፲፩. እንደአስፈላጊነቱ ተመሳሳይ የምክር ቤት አደረጃጀት በክፍለ ከተማና በወረዳ ደረጃ እንዲቋቋም ያደርጋል፤ ስልጣንና ተግባራቸውንም ይወስናል፤

፲፪. የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወ ጣል፤

፲፫. ከብሄራዊ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲. ??? ????? ?? ? ????? ????

የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በከተማው ከንቲባ የሚሰየም ሰብሳ ቢና ፀሐፊ ጨምሮ ከ ፯ የማያንሱ ዓባላት ይኖሩታል፤ ተጠ ሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩. የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ከተማ አቀፍ ሥራዎችን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ይገመግማል፤የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ያስቀምጣል፤ ለእቅዱ ተፈጻሚነት ትኩረት ሰጥቶ ያስተባብራል፤



5. Create conducive environment in all public forums and organs to encourage saving culture;
6. Make additional revenue be generated by using bond sales and public participation in our city;
7. Notifay the amount of money collected in the City for the construction of the grand renaissance dam in consultation with the Federal Government and National Council;
8. Ensure the City's Grand Renaissance Dam construction revenue collrctione procedure is in compliance with the National Council Revenue Collection Procedure;
9. Enable the public to create national consensus and perform the duty of dissolving any kind of anti-developmental forces organized to be an obstacle to the construction of the dam;
10. Establish ad hoc, standing or sub-committees necessary for the implementation of the objective, listen report of the same;
11. Cause the establishment of similar council organization in sub- cities and wereda's where necessary; Determine power and duties of the same;
12. Issue directives that determine its meeting procedure;
13. Perform other activities as may be given to it by the National Council;

## 10. Powers and Duties of the Executive Committee.

The Executive Committee shall consist of not less than 7 members including chairman and secretary appointed by mayor of the city. Accountable to the Council and shall have the following powers and duties:

1. Evaluate city wide short and long term plan for the construction of the Ethiopian Grand Renaissance Dam, provide performance direction, and coordinate same, giving focus to the implementation of the plan;

፪. እቅዱን ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ ኮሚቴዎችን በመ ንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣በግል ተቋ ማት፣እና የተለያዩ አደረጃጀቶችን ያቋቁማል፤ ኃላፊነ ታቸውን በትክክል መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ይቆ ጣጠራል፤

፫. እቅዱን ለማስፈጸም በየደረጃው የተቋቋሙ ኮሚቴ ዎችን የግንኙነት ጊዜ አስቀምጦ የሥራ እንቅስቃ ሴያቸውን ወቅታዊ ሪፖርት ያዳምጣል፤እንዲሁም እንደኮሚቴ ያከናወናቸውን ተግባራት በጋራ ይገመ ግማል፤ ወርሃዊ ሪፖርት ለከተማው ከንቲባና ለምክር ቤቱ ሰብሳቢ ያቀርባል፤

፬. ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ገቢ ማስገኛ የተጣለውን ግብ ተግባራዊ ለማድረግ የቦንድ ሽያጭና የህዝባዊ ተሳ ትፎ እንቅስቃሴን ያስተባብራል፤ተግባራዊነቱንም ይከ ታተላል፤

፭. ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን በትውስት የሚመጡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

**፲፩. ?? ?? ?? ???? ????? ????**

፩.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ መሰረት ለምክር ቤቱ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት በአግባቡ መፈጸ ማቸውን ያረጋግጣል፣ በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

፪.የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

፫.የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ይሰራል፡፡

፬.የምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፡፡

፭.በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ ንኡስ አንቀጽ ፲ መሰረት ለሚ ቋቋሙ ኮሚቴዎች ሰብሳቢ ይሰይማል፡፡

፮.ምክር ቤቱን በመወከል ግንኙነት ያደርጋል፡፡

፯.ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ አካላት ኃላፊዎችን ይሰይ ማል፡፡

፰.የምክር ቤቱን ውሳኔ አፈጻጸም ይከታተላል፡፡

2. Establishe committee in governmental and non-governmental organizations, private organs and other forums necessary for the implementation of the plan, follow up their performance, supervise same;

3. State meeting schedule to listen to performance report of the committee established for the implementation of the plan and jointly evaluate duties done as committee, present monthly report to the mayor and chair man of the council;

4. Coordinate public participation and bond sales for the practical application of revenue generation for the construction of the renaissance dam, follow up implementation of the same;

5. Facilitate conditions for secondment of necessary staffs from governmental or non-governmental organizations.

**11. Powers and Duties of the Chairman of the Council**

1. Insure the proper execution of the powers and duties of the council provided under Article 9 of this Regulation, supervise same.
2. Preside over the meetings of the council.
3. Perform as chairman of the executive committee.
4. Call extraordinary meetings of the council.
5. Appoint chairman for committee's established under Article 9 sub-articles 10 of this Regulation.
6. Communicate on behalf of the council.
7. Appoint heads for organs accountable to the council.
8. Follow up the implementation of decisions of the council.

፱. የምክር ቤቱን የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድና በጀት ለምክር ቤቱ በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡

፲. በየሩብ ዓመቱ እና በየስድስት ወሩ የምክር ቤቱን የዕቅድ ክንውን አፈጻጸም ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

፲፩. በምክር ቤቱና በብሔራዊ ምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

**፲፪. ?? ?? ?? ? ??? ????**

፩. ሰብሳቢው በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ ለሰብሳቢው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

፪. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ በመሆን ይሰራል፡፡

፫. በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከና ወናል፡፡

**፲፫. ?? ?? ?? ?? ? ????? ????**

፩. ጽሕፈት ቤቱን ያደራጃል፤ ለጽሕፈት ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ ሰራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፪. የምክር ቤቱን የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ እንዲሁም በጀት ያዘጋጃል፤ሲጸድቅና ሲፈቀድም ተግባ ራዊ ያደርጋል፡፡

፫. ለምክር ቤቱ የሚቀርቡትን አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፡፡

፬. የምክርቤቱን ቃለ ጉባኤዎች ይመዘግባል፣ ይይዛል፡፡

፭. ምክር ቤቱን የሚመለከቱ ሰነዶች መያዛቸውን ያረጋ ግጣል፡፡

፮. ያለ ድምጽ በሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ ስብሰባ ይሳተ ፋል፡፡

፯. በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከና ውናል፡፡

**፲፬. የምክር ቤቱ አባላት መብት**

ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል:-

፩. በምክር ቤቱ ስብሰባ የመሳተፍና ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ፤

፪. በምክር ቤቱ በሚደራጁ ቋሚ፣ ጊዜያዊ ወይም ንዑሳን ኮሚቴዎች በአባልነት የመሳተፍ፤

9. Present to the council long and short term plan and budget of the council.
10. Present to the council three month and six month plan performance evaluation of the council.
11. Perform other activities as may be given to him by the council and National Council.

**12. Powers and Duties of the Deputy Chairman**

1. Perform on behalf of the chairman powers and duties provided under Article 11 of this Regulation in case of absence or incapacitaion of the chairman;
2. Perform as secretary of the executive committee;
3. Perform such other activities as may be assigned to him by the chairman.

**13. Powers and Duties of the Secretary of the Council**

1. Organize the office, employ necessary staffs with, administer same;
2. Prepare long and short term plan and budget, implement same upon approval;
3. Prepare agenda's to be presented for the council in consultation with the chairman;
4. Record, properly organize and keep minutes of the council;
5. Ensure relevant documents regarding the council are kept;
6. Participete without a vote on meeting of the excutive committee;
7. Perform other activities as may be assigned to him by the chairman.

**14. Right of Members of the Council**

Any members of the council shall have the right to፡

1. Participate in the meeting of the council and express his opnion freely;
2. Participate in the standing, ad hoc or sub-committee that may be established by the council;

፫. በምክር ቤቱ የሚተላለፉ ውሳኔዎችን የማወቅ መብት ይኖረዋል፡፡

3. To know the decisions passed by the council.

## ፲፭. የምክር ቤቱ አባላት ግዴታ

ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል፡-

፩. በምክር ቤት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ በሰዓቱ የመገኘት፣
፪. በምክር ቤቱ በሚደራጁ ቋሚ ጊዜያዊ ወይም ንዑሳን ኮሚቴዎች በአባልነት የመስራት፣
፫. በምክር ቤቱ በሚደራጁ ቋሚ፣ ጊዜያዊ ወይም ንዑሳን ኮሚቴዎች አገልግሎት በነፃ የመስጠት፣
፬. ምክር ቤቱ በሚስጥር እንዲጠበቁ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች ሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 15. Duty of Mebers of the Council

Any members of the council shall have the duty to:-

1. Be present timely to the council's regular or extraordinary meetings;
2. work as a member of the standing, ad hoc or sub-committee's established by the council;
3. Give pro service to the standing, ad hoc or sub-committee's established by the council;
4. Keep the secret of the decisions passed to be confidentially by the council.

## ፲፮. ?? ?? ?? ????? ? ?-? ???

፩. ምክር ቤቱ በየሦስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
፪. ማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
፫. የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚያልፈው በስብሰባው ከተገኙ የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ሲደገፍ ይሆናል፡፡

## 16. The Councils Meeting Procedures

1. The council regular meetings shall be held every three months; The chairman of the council may call an extraordinary meeting if necessary.
2. In every meeting, the presence of more than half of the members of the council constitutes a quorum.
3. Decisions of the council require the approval of majority of members attended on the meeting.

# ክፍል አራት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፲፯. በጀት

፩. በከተማ አስተዳደሩ የሚመደብ በጀት፣
፪. ከዕርዳታ እና ስጦታ፣እንዲሁም
፫. ከልዩ ልዩ የገቢ ምንጮች የሚሸፈን ይሆናል፡፡

## ፲፰. ስለ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ

፩. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
፪. የጽሕፈት ቤቱ ሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በአስተዳዳሩ ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡

# PART FOUR
# MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 17. Budget

1. Budget allocated by the City Government;
2. From donation, gift and;
3. From other revenue sources.

## 18. Books of Accounts

1. The office shall keep complete and accurate books of accounts;
2. The books of accounts and financial documents of the office shall be audited by the City Government Auditor General or by auditors assigned by him.

፲፱. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፳. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከግንቦት ፳፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**ግንቦት ፳፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**19. <u>Power to Issue Directives</u>**

The executive committee may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

**20. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come into force on the 2nd day of June, 2011.

**Done at Addis Ababa**
**On this day of 2nd June, 2011**

**Kuma Demeksa**
**Mayor of Addis Ababa City**